# የግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ደረጃ 2 ሪፖርት የመንግስት ምላሽ፡ አመታዊ ሪፖርት 2026

የካቲት 25 2026

## ይዘቶች

የግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ደረጃ 2 ሪፖርት የመንግስት ምላሽ፡ አመታዊ ሪፖርት 2026 .....1
የሚኒስትር መቅድም .....2
የአስፈፃሚ ማጠቃለያ .....3
ከዚህ ሪፖርት ጋር በመታተም ላይ የሚገኙ ተያያዥ ማስታወቂያዎች እና ሰነዶች .....6

# የሚኒስትር መቅድም

ሰኔ 14 2017 ግሬንፈል ታወር ላይ የተከሰተው ቃጠሎ የ72 ሰዎችን ህይወት አሳጥቷል። ለቀጣይ ዓመታት የቤተሰቦች፣ ማሕበረሰብ እና ሀገራችን ጠባሳ ሆኖ ይቆያል። ቤተሰቦቻቸውን ያጡ፣ ከአደጋው የተረፉ እና ሰፊው የኖርዝ ኬንሲንግተን ማሕበረሰብ ያሳዩት ብርታት እና ጽናት ብዙዎችን የሚያነቃቃ ሆኖ ይቀጥላል።

ይህ አሰቃቂ አደጋ እንዲፈጸም ያደረገው የመንግስት አባላት፣ ኢንዱስትሪው እና ተቆጣጣሪዎቹ የፈጸሙት ድክመት በፍጹም ሊኖር የማይገባው እንደነበረ በአእምሯችን ምንግዜም ልንይዘው ይገባል። ይህ አሰቃቂ አደጋ፡ ሊከላከሉት የሚቻል ነበር እንዲሁም መካላከል ይገባውም ነበር። ያላፈውን መለወጥ የማንችል ቢሆንም፡ ግን የሚያስተምረንን በቀናነት መጋፈጥ፣ በወሰኝነት መተግበር እንሲሁም ይህ እጅግ ከባድ ድክመት በፍጹም እንዳይደገም መስራት እንችላለን።

የግሬንፈል ማጣሪያ ያቀረባቸውን ሁሉንም ምክረሃሳቦች መንግስት ተቀብሏል ግን ደግሞ፡ነዋሪዎች የጠየቁትንን እና የሚገባቸውን ወጥነት ያላቸው፣ የረጅም ጊዜ ለውጦችን ለማምጣት - እንደ ግሬንፈል አሰቃቂ ክስተት ቀጥተኛ ውርስ - በሁሉም የአገሪቷ ክፍል የሚገኙ ሰዎች፣ እና የማህበራዊ መኖሪያ ቤት ተከራዮች በተለይ ደህንነት ባላቸው፣ የተሻሉ መኖሪያዎች እንዲኖሩ ሰፊ ትጋት አድርገናል። ሰዎችን በማስቀደም፣ መከላከያዎችን በማጠንከር እና ህንጻዎችን የማርቀቅ፣ የመገንባት እና የማስተዳደር ሃላፊነት ያለባቸው ከፍተኛውን የደረጃ ጥራት እንዲያሟሉ በማድረግ ታማኝነትን እንገነባለን።

የግሬንፈል ታወር ማጣሪያውን ተከትሎ የወጣው የመጀመሪያው ዓመታዊ ሪፖርት፡ ያከናወንናቸውን ስራዎች ይዘረዝራል፡ ተበለጠ ጠንካራ ቁጥጥር፣ በግንባታ ውጤቶች ማሻሻያ ላይ እርምጃዎች፣ በተሻለ መልኩ የጠራ መመሪያ፣ ከፍተኛ የባለሙያ ደረጃዎች፣ የተሻሻሉ አፈጻጸሞች፣ ፈጣን ማስተካከያዎች እና ለድንገተኛ ሁኔታዎች የተሻለ ዝግጅት።

ግን ብዙ ሊሰራ የሚገባ ይቀራል። አንዳንድ ለውጦች የሕግ ማርቀቅ ይጥይቃሉ፣ ሌሎች ቀጣይነት ያለው የባህል ማሻሻያ ይጠይቃሉ። ሁለቱንም ለማሳካት ተግተን እንሰራለን። መታሰቢያ ኰሚሽን እና ማሕበረሰብ ዘለቄታ ያለው መታሰቢያ እያቀዱ ስለሆነ ለማገዝ በቅርበት መስራታችንን እንቀጥላለን። ያንን መታሰቢያ በገንዘብ ለማገዝ ሕጋዊ ስልጣን የሚያሰጠንን ሕግ ስናጸድቅ፡ የሚቀጥሉት ሳምንታት በዚያ የሂደት አስፈላጊ እርምጃዎች ይታያሉ።

ሰዎች በቤታቸው ደህና እንዲሆኑ እና ደህንነት እንዲሰማቸው የማድረግ ሃላፊነት አለብን እንዲሁም ከዚህ ቀደም ያንን ደህንነት ያቃለሉ ድክመቶች ፈጽሞ ደግመው አይከሰቱም። ለስራው ያለን ቁርጠኝነት አይደናቀፍም።

### የተከበሩ ስቲቭ ሪድ ኦቢኢ ኤምፒ

የመኖሪያ፣ ማህበረሰብ እና አካባቢ መስተዳድር የመንግስት ጸሓፊ

# የአስፈፃሚ ማጠቃለያ

1. የግሬንፈል ታወር አሰቃቂ ክስተት ፈጽሞ ሊከሰት የማይገባው ፍጻሜ ነበረ፣በቃጠሎው ምክንያት፡ 72 ንጹሀን ሰዎች ደህንነት ሊሰማቸው በሚገባ እና ደህና በሆኑበት ስፍራ ላይ ህይወታቸውን አሳጥቷል።

2. መንግስት የግሬንፈል ታወር ማጣሪያ ደረጃ 2ን ምላሽ ከሰጠ አንድ ዓመት አልፏል፡ ቀኑ በአሰቃቂው አደጋ እጅግ የተጠቁ ሰዎች በከፍተኛ እና አስፈሪ ትውስታዎች እንዲሸፈኑ ያደረገ ነው።

3. የግሬንፈል ታወር፣ላንካስተር ዌስት ኢስቴት እና የኖርዝ ከንሲንግተን ማህበረሰብ፡ ማሻሻያ ተደርጎ ለማየት በማይናወጥ ትጋት ቀጥለዋል እንዲሁም ይህ መንግስት ትርጉም ያላቸውን እና ዘላቂ ለውጦችን ለመተግበር ትጋቱን ቀጥሏል።

4. ሰር ማርቲን ሙር ቢክ እና ቡድኑ በማጣሪያው ደረጃ 2 ላይ የሰሩት ስራ 58 ምክረሃሳቦች እንዲዘጋጁ አስደርጓል። መንግስት እና ሌሎች የሚመለከታቸው ድርጅቶች ሁሉንም ምክረሃሳቦች ተቀብለዋል።

5. ለማጣሪአው ምላሽ ለመስጠት፡ መንግስት፣ አንዳንድ ምክረ ሃሳቦች አዲስ ህጎች ተረቀው እንዲጸድቁ ስለሚያስፈልጋቸው ቢያንስ አራት ዓመት እንደሚወስድ ታሳቢ በማድረግ፡ እነዚህን ለመተግበር ዕቅድ አአጥቷል፣ በሁሉም ምክረሃሳቦች ላይ ስራ እየተካሄደ ነው እንዲሁም በዚያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ በመስመራችን እንቀጥላለን።

6. ከየካቲት 25 2026 ጀምሮ፡ መንግስት በምክረሃሳቦች ተግባር፣ መጠናቀቅ እና በመደበኛ መንገድ መዝጋት 12 በተመለከተ ሪፖርት አቅርቧል ፤ ከደረጃ 1 ምክረሃሳቦች የቀሩትን ሁለቱንም ጨምሮ። እስከ 2026 ማብቂያ ድረስ የምክረሃሳቦች 70% ይዘጋሉ ብለን እንጠብቃለን።

| **የውይይት ርዕሰ ጉዳይ** | **የምከረ ሃሳቦች ቁጥር** | **በሂደት ላይ ያለ** | **የተፈጸመ** |
|---|---|---|---|
| የግንባታ ኢንዱስትሪ | 28 | 24 | 4 |
| የእሳት እና ማዳን አገልግሎቶች | 13 | 9 | 4 |
| ምላሽ እና ማገገም | 14 | 14 | 0 |
| ለአደጋ ተጋላጭ ሰዎች እና ደረጃ 1 ምክረ-ሃሳቦች | 6 | 2 | 4 |
| **ድምር** | **61** | **49** | **12** |

7. የሂደት ሪፖርት ግንቦት፣ መስከረም እና ታሕሳስ 2025 ላይ ታትመው ነበር፤ እያንዳንዱን ምክረሃሳብ ለማስፈጸም የተሰሩ ስራዎችን እና የሰፊ ማሻሻያ ቁልፍ እድገቶችን በተመለከተ በዝርዝር ያቀረቡ ነበሩ።

8. የሚቀጥለው ዓመታዊ ሪፖርት፡ባለፈ ዓመት ስለተሰሩ ስራዎች ዝርዝር መረጃዎችን፣ በቀጣይ ዓመት እና በኋላ ስላሉት መሰረቶች እና እና ዕቅዶች ጨምሮ በዝርዝር ይገልጻል። ነዋሪዎችን የሚከላከል እና የህንጻዎች ደህንነት የሚያረጋግጡ የግንባታ አሰራር እንዲኖር፡ ሲስተሙን እና ሂደቱን ለማጠናከር በመሰራት ላይ ያሉትን ያንጸባርቃል። ሪፖርቱ በጭብጥ ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን ከየካቲት 2025 የመንግስት ሪፖርት ጋር የሚተካከል ነው እንዲሁም በእያንዳንዱ ምክረሃሳብ ላይ ስለተደረገው መሻሻል፡ ክፍት ሆነው ለቆዩ ምክረሃሳቦች የማስፈጸሚያ የጊዜ ገደብ ጋር አዲስ መረጃ የያዘ አባሪ ይኖራል።

9. የ2025 ቁልፍ መሻሻሎች እና እድገቶች የሚከተሉትን ይይዛሉ፡

10. **የህንጻዎችን እና የእሳት ደህንነት ሲስተሞችን ማጠናከር**። ባለፉት ዓመታት፣በበለጠ ወጥነት ያላቸው እና ተጠያቂ የቁጥጥር ማዕቀፎችን በተመለከተ ሊታዩ የሚችሉ መሻሻሎችን አድርገናል። የህንጻ ደህንነት። የእሳት ደህንነት እና የድንገተኛ ምላሽ ተግባሮችን በአንድ ክፍል መሪነት ውስጥ እንዲካተቱ አድርገናል፡ ይህም የበለጠ ቀጣይ የአደጋ ስጋት ቁጥጥር እንዲኖር እንዲሁም ለቁጥጥር እና ማስፈጸም በተሻለ መልኩ የተወሃሃደ አገባብ እንዲኖር ያስችላል። ጥር 27 2026 ላይ የግንባታ ደህንነት ተቆጣጣሪ (BSR) የራሱን ህጋዊ መልክ ይዞ ተቋቁሟል፣ ከጤና እና ደህንነት ስራ ማስፈጸም በመኖሪያ፣ ማህበረሰብ እና አካባቢ መስተዳድር ስር ወደ ሰፊ አካልነት ተሸጋግሯል ይህም ነጠላ የግንባታ ተቆጣጣሪ እንዲኖር መሰረት ያስያዘ ነው። የግንባታ ደህንነት ተቆጣጣሪ (BSR)፡ በግንባታ አስራር ላይ የባህል እና የብቃት ደረጃዎች መሻሻል እንዲኖር አስችሏል እንዲሁም አሁን መንግስት ከፍተኛ ስጋት ያለባቸውን ህንጻዎች - በተገቢው እና ውጤታማ መንገድ መስራታቸውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ እርምጃዎችን እየወሰደ ይገኛል። ከእንቅስቃሴው ጐን ለጎን፡የግንባታ ቴሌኮምዩኒኬሽን ስራዎች ቁጥጥርን ለመተግበር ምክክር ተጀምሮ ነበር፣ ፕሮፖዛሉ በአሰራሩ ላይ ያለውን ጫና ማቃለል ላይ ያግዛል፣ ቀጣይነትን ያሻሽላል እንዲሁም የግንባታ ደህንነት ተቆጣጣሪ (BSR) ልዩ እውቀት በጣም ውስብስብ እና ከፍተኛ የአደጋ ስጋት -ባላቸው ስራዎች ላይ ማድረጉን ያረጋግጣል። እነዚህ ለውጦች፡መመሪያ እና እውቀት የበለጠ ወደሚፈለግባቸው ማነጣጠራቸውን ለማረጋገጥ፣ ይህንን እያደረገ እያለም የቁጥጥር ልምዶችን እና የኢንዱስትሪውን ብቃት ወደ አንድነት ለማምጣት የመንግስትን ቁርጠኝነት ያንጸባርቃሉ።

11. **ሰፊ የአሰራር ማሻሻያ በግልጽ ሕጎች እና የሚጠበቁ [ውጤቶች]** ደህንነቱ የተጠበቀ ንድፍን፣ የህንጻዎች ግንባታ እና ቁጥጥርን ቅድሚያ የሚሰጡ ህጎችን ማጠናከራችንን ቀጥለናል። በዚህ ዓመት ስራችን፡ የሚጠበቁ ውጤቶችን ግልጽ ማድረግ ላይ እንዲሁም በማጣሪያው ተለይተው የታወቁ ክፍተቶችን መሙላት አተኩሯል፡ ይህም በሚቀጥሉት የተግባር ደረጃዎቻችን በፍጥነታችን እንድንቀጥል ለማስቻል ነው። ይህም ከዚህ ሪፖርት ጎን ለጎን የታተመውን እና ምርቶቹ በተገቢ ሁኒአታ እንዲመረመሩ፣ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማረጋገጥ ላይ ያለመ ቁጥጥርን ለማጠናከር ሁለገብ ለውጦች እንዲኖሩ እና የቁጥጥር ክፍተቶችን እንዲዘጉ ሃሳብ የሚያቀርበውን የግንባታ ምርቶች ማሻሻያ ነጭ ወረቀትን ያካትታል። የግንባታ ምርቶች ማሻሻያ ፍጥነቱን ለማስቀጠል ከነጩ ወረቀት ጎን ለጎን ቁጥትር የማይደረግባቸውን ምርቶች ወደ ቁጥጥር አሰራሩ እንዲገቡ ለማድረግ በአጠቃላይ የደህንነት መመዘኛዎች ምክክር እያዘጋጀን ነው። በዚህ ዓመት ወደ በኋላ ሁለተኛውን ሕግ ወደፊት

ለማቅረብ እናስባለን። በተጨማሪም፡በህግ የተቀመጡ የግንባታ ደህንነት መመሪያዎች መሰረታዊ ግምገማ የማከናወን ስራ ይቀጥላል። የግንባታ ደህንነት ተቆጣጣሪ (BSR)፡ይህንን ግምገማ ቅርጽ ማስያዝ ጀምሯል፣ በሰፊው ከዘርፉ ጋር እየተባበረ ነው እንዲሁም ሓምሌ 2025 ላይ ግምገማውን ለማገዝ እና መረጃ ለመምገብ የባለሙያዎች ቡድን ሹሟል። ግዜያዊ ሪፖርት በጸደይ 2026 ላይ ይጠበቃል።

12. **በግንባታ ስራ ዘርፍ ውስጥ ብቃትን እና አቅምን ማሳደግ።** የካቲት 2025 ላይ የተገባውን ቃል በመከተል የሙያ ብቃት ደረጃዎችን ለማሻሻል በቡሉም የግንባታ፣ የእሳት ምህንድስና ፣ እና የቃጠሎ ስጋት ግምገማ ላይ ጉልህ እርምጃዎችን ወስደናል። ማጣሪያው በጠየቀው መሰረት ማለፊው ዓመት የቴክኒክ አማካሪ፣ የብቃት ደረጃ አዲስ አካሎች ማእቀፎች እና በዘርፍ ደረጃ ትብብሮች አካላት የበለጠ ጠንካራ፣ የበለጠ ቀጣይነይ ያለው የሙያ ባህል ማስቀመጥ ጀምረዋል። ከዚህ ጎን ለጎን፡ጥያቄ በበዛባቸው ዘርፎች የስራ ሓይሉን ዓቅም ለማስፋት ትኩረት የተደረገባቸው ኢንቨስትመንቶች ጀምረዋል። 2025 ውስጥ በእሳት ምህንድስና፣የህንጻ ቁጥጥር እና ግንባታ ዘርፍ ከ 1200 በላይ ባለሙያዎች የአዲሱን ማዕቀፍ የብቃት ስልጠና ተከታትለዋል። አሁን የእሳት ምህንድስና አማካሪ ቡድን (ፓናል)፡ የብቃት ደረጃ መልእክት፡የተሻሻሉ ዲግሪዎች እና የ ሲ ፒ ዲ ፍኖቶች ግብአት በመሆኑ በ 35 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተቀባይነት አግኝቷል። የግንባታ ቁጥጥር ገለተኛ ቡድን (ፓናል)፡ለ2926 እንዲፈጸሙ የተባሉ ምክረሃሳቦችን ቅርጽ ለማስያዝ ከ 220 በላይ የማስረጃ ጽሑፎችን ገምግሟል ።

13. **ተጠያቂነትን ማሻሻል እና አፈጻጸምን ማጠናከር** የብቃት ደረጃዎች በማይሟሉብት ጊዜ የሰዎችን ደህንነት የማስጠበቅ ሃላፊነት ያለባቸው አካላት ተጠያቂ መሆናቸውን ማረጋገጥ ላይ አተኩረናል። ባለፈው ዓመት፡ መንግስት አዲስ የቁጥጥር መሳሪያዎችን አውሃህዷል፣ የማስፈጸም አቅም አስፍቷል እንዲሁም የተሻሻሉ የክትትል ብቃት አሰራሮችን አስቀምጧል። ይህም የደህንነት ስጋት በማያቋርጥባቸው ላይ አዲስ የእገዛ መንገዶችን መመስረት እንዲሁም የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች በበለጠ ግዜውን የጠበቀ እና ውጤታማ እርምጃ እንዲወስዱ መደገፍን ያጠቃልላል። ባለፈው ዓመት፡ አስቀድሞ ከነበረው ዓመት ጋር ሲወዳደር የአካባቢ መስተዳድር 124% ተጨማሪ መደበኛ ማስጠንቀቂያዎችን እና 140% ተጨማሪ ቁጥጥሮችን አካሄዷል። የጋራ ቁጥጥር ቡድን ከ110 በላይ የህንጻ ግምገማዎች አግዟል በዚህም የአደጋ ስጋት ባልተፈታባቸው 15 የማስፈጸም ስራዎች እንዲካሄዱ አድርጓል። የማስተካከል ተፈጻሚነት ክፍል እስከ መጋቢት 2026 ባለው ግዜ ውስጥ ሙሉ የሰው አቅም ይኖረዋል፡ ይህም ከፍተኛ ስጋት ባለባቸው ህንጻዎች ቀጥተኛ እገዛ እንዲኖር ያደርጋል።

14. **ነዋሪዎችን መደገፍ እና ድምጻቸውን ወደ መሃል ማውጣት።** ከየካቲት 2025 ጀምሮ ዋናው ቅድሚያ የተሰጠው የነዋሪዎችን መብት ማጠናከር፣ ግልጽነትን ማሻሻል እና ችግሮች በፍጥነት እና በክብር መፈታታቸውን ማረጋገጥ ነበር። ባለፉት 12 ወራት፡የታለፉ ተሞክሮዎች የፕሊሲ ግንባታ ላይ በቀጣይነት ማበርከታቸውን ለማረጋገጥ፡ ማህበራዊ መኖሪያዎች ላይ ለውጦችን ወደፊት አስቀድመናል፣ ለነዋሪዎች አስተያየቶች መንገድ አጠናክረናል፣ የነዋሪዎች ስልጠና እና ድጋፍን አስፍተናል እንዲሁም በግሬንፈል ታወር አሰቃቂ አደጋ ከተጠቁት ጋር መስታራችንን ቀጥለናል። ባለፈው ዓመት ውስጥ፡እንዲሰፋ የተደረገው የነዋሪዎች ቡድን (ፓነል) በግልጽነት እና ቅሬታ መፍታት ጉዳዮች አያያዝን ጨምሮ፡ ከ20 በላይ ፖሊሲዎች ላይ በቅጥታ እያበረከተ እያለ፡ ከ4500 በላይ ነዋሪዎች መንግስት

በገንዘብ በደገፋቸው ፕሮግራሞች አማካኝነት ስልጠና እና የሙብት መረጃዎችን ተካፍለዋል። ነገሮችን ትክክል እናድርግ የሚለው ዘመቻ 1.8 ሚልዮን ወደ ሚሆኑ ተከራዮች ተዳርሷል፤ ይህ ሪፖርት የሚዘጋጅበት የመጀመሪያ ግዚዎች አካባቢ ላይም [ቁጥሩ] ጨምሯል።

15. **የተፋጠኑ ማስተካከያዎች እና በተጠቁ ህንጻዎች ውስጥ ለሚኖሩ የሚሰጥ ድጋፍን ማሻሻል።** አደገኛ የደህንነት ስጋት ያሉባቸውን ቤቶችን ደህንነታቸው እንዲጠበቅ ማድረግ የስራችን ማእከላዊ ትኩረት መሆናቸውን ማረጋገጥ። ባላፈው ዓመት፡ የማስተካከል ስራዎች እንቅፋቶችን ለማስወገድ እርምጃዎችን ወስደናል፣ ደህንነት ለጎደለባቸው ህንጻዎች ሃላፊነት የሚሸከሙትን ተጠያቂነት አጠናክረናል እንዲሁም መዘግየት እና እርግጠኝነት ማጣት ያሰቸገራቸውን ነዋሪዎች ደግፈናል። በታህሳስ 2025 መጨረሻ ላይ፡ 2168 ህንጻዎች የማስተካከል ስራዎች ጀምረዋል ወይም አጠናቀዋል፤ሙሉ በሙሉ የተፈጸሙትን 1475 ጨምሮ። በገንቢዎች ውል ከተሸፈኑት ህንጻዎች ውስጥ 93% በማስተካከል ፍኖት እንዳለፉ እና 41% የተረጋገጠ ችግሮች ባሉባቸው ህንጻዎች ስራ መጀመሩን ወይ መጠናቀቁን ገንቢዎች አረጋግጠዋል። የርብራብ (ክላዲንግ) ደህንነት ዕቅድ፡ የሁሉም ባለ አራት ፎቅ+ የካርታ ወይ ስእል ዳሰሳ ጥናት መረጃ መዝገብ የመጀመሪያ ግምገማ አካሄዷል። ይህ ሪፖርት የተደረጉ መሻሻሎችን፣ የተጠናከረ የቁጥጥር ስልጣንን ጨምሮ፣ የቁጥጥር አዲስ መንገዶች እንዲሁም የማስተካከል ብቃት እና ፍጥነትን ለማሻሻል ከኢንዱስትሪው ጋር የሚሰሩ ስራዎችን ይዘረዝራል።

16. **ብሄራዊ ጽናት መገንባት እና የድንገተኛ ዝግጁነትን ማሻሻል።** በዚህ ዓመት፡ የአካባቢ እና ብሄራዊ ውህደት ማሻሻል ላይ በማተኮር፣ የደረጃ 1 ምላሽ ሰጪዎችን ድርሻ በማጠናከር እንዲሁም ለአደጋ ተጋላጭ ነዋሪዎች ፍላጎቶች በዕቅድ እና ዝግጁነት ላይ ማእከላዊ ቦታ መያዛቸውን በማረጋገጥ፡ከድንገተኛ ምላሾች ጋር በተያያዘ የማጣሪያው ምክረሃሳቦችን ሰርተንባቸዋል። የዘመነ ብሄራዊ መመሪያ እና የበለጠ ግልጽ ተጠባቂ ውጤቶች ለሸርኮች፡ የተወሳሰቡ ድንገተኛዎች ሲኖሩ በተሳካ ሁኔታ ምላሽ የሚሰጥ የበለጠ ጽኑ አሰራር እንዲኖር ያግዛል። 2025 ውስጥ፡ ከ2000 በላይ ነዋሪዎች ከዘመነው ብሄራዊ ጽናት ደረጃዎች እና አምበር ቡክ ጋር ተስማሚ የሆነ አዲስ ስልጠና ተከታትለዋል። አምስት የአካባቢ ጽናት ፎረም ቀዳሚ ቦታዎች በአሁኑ ጊዜ የተወሃሃደ ጽናት አመራር ሞዲሎች ሙከራ እያካሄዱ ሲሆን የመጀመሪያዎቹ ግኝቶች ለ2026 በጋ ይቀርባሉ። በተሻሻለው የአካባቢ መስተዳድር በሕግ ከተሰጠው ግዴታ በሚጠበቁ ውጤቶች ጋር ለአደጋ ተጋላጭ ነዋሪዎች እገዛ የተሻሻለ መመሪያ ሚያዚያ 2025 ላይ ተዘጋጅቷል።

## ከዚህ ሪፖርት ጋር በመታተም ላይ የሚገኙ ተያያዥ ማስታወቂያዎች እና ሰነዶች

17. መንግስት፡የግሬንፈል ታወር መታሰቢያ ግንባታ እና ጥገና ለማስቻል በአጭር ጊዜ ውስጥ የሕግ አዋጅ እንደሚያወጣ አሳውቋል። ይህ መታሰቢያ፡ ህይወታቸው ያጡትን እና በአስቃቂው አደጋ ህይወታቸው ለዘላለሙ የተቀየረባቸውን ሰዎች ያከብራል። የክብር እና የሰላም ቦታ፣ ሰዎች የሚያስታውሱበትን፣ የሚወያዩበት እና አክብሮታቸውን የሚገልጹበት ይሆናል። ገለልተኛው ቡድን (ፓናል) ባቀረበው ምክረሃሳብ መሰረት፡በተጨማሪም በአሰቃቂው አደጋ ተጽእኖ ለተፈጠረባቸው ሰዎች የግል እና የተከበረ የመታሰቢያ ቦታ ይዘጋጃል። መንግስት፡ዘላቂ መታሰቢያ መስራት

እና መትከል ላይ፣ ተጽእኖ የደረሰባቸው ሰዎች እና በአሳዛኝ ሁኔታ ህይወታቸውን ያጡ ሰዎች ፈጽሞ እንዳይረሱ ገለልተኛ የግሬንፈል ታወር መታሰቢያ ኮሚሽንን እና ማህበረሰቡን ለመደገፍ ቁርጠኛ ነው።

18. መንግስት፡ የግንባታ ምርቶች ማዕቀፍ ለማጠናከር እና የበለጠ ግልጽ እና ታማኝ አሰራር መኖሩን ለማረጋገጥ ከፍተኛ መሻሻሎች የሚደረጉበት ፕሮግራም ወደፊት እያወጣ ይገኛል። ለግንባታ ምርቶች ማሻሻያ አረንጓዴ ወረቀት ምላሽ ለመስጠት፡ መንግስት በተሻሻለ ደህንነት እና ተጠያቂነት ላይ ያተኰሩ ግልጽ ፖሊሲዎችን እና ቀጣይ እርምጃዎችን የሚዘረዝር ነጭ ወረቀት አዘጋጅቷል፡ በተጨማሪ ለውጡን ለመምራት፡ መንግስት ቁጥጥር የማይደረግባቸውን ምርቶች ወደ ቁጥጥር አሰራሩ ለማስገባት፣ ከዕቅዶች ጋር፣ በምክርቤት ግዜ ላይ የሚመረኰስ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ህግ በዚህ ዓመት ውስጥ ለማወጅ  በአጠቃላይ የደህንነት መመዘኛዎች ላይ ምክክር እያካሄደ ነው።

19. ይህ መንግስት፡ ነዋሪዎች በመኖሪያቸው ደህንነት እንዲሰማቸው፣ የሚጠበቁ ውጤቶች ግልጽ እና ተጠያቂ እንዲሁም ኢንዱስትሪው ሃላፊነቱን እንዲወጣ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን እንዲይዝ ማድረግ ላይ ማተኰሩን ይቀጥላል። ይህ ሁሉንም ተቀባይነት ያላቸውን ምክረሃሳቦች መተግበር እና ወደ ግረንፌል ታወር አሰቃቂ አደጋ የመሩ ድክመቶች እንዳይደገሙ ማረጋገጥ ላይ ያለንን ተነሳሽነትን ያጎላል።